የረቡዕ ታህሳሥ 12 1998 ዓ.ም ( የዲሴምበር 21 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## በጋራ ሀገር በጋራ ለመኖር

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት፥ ተከፍቶም ይሁን ተደስቶ፥ ሠላምም ሆኖ ሠላም አጥቶ፥ በውጭ ጥቃትም ጊዜ ይሁን፥ በወገን ጭቆና አገዛዝም አብሮ ኖሯል። ከጥንቱ ከጧቱ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመኖሩ ማዕከላዊ ነጥቡ የጋራ ሀገሩ ነበረች። አሁንም ነች። ወደፊትም እርሷው ነች። በጋራ ሀገሩ ደግሞ በጋራ ኖሯል። በዚህ መሠረታዊ ዕምነቱ ይመስለናል ዛሬ፥ ለፖለቲካ ድርጅቶችን በመላ፥ እንደ ፖለቲካ ድርጅትነታቸሁ፥ መስማማት ካልቻላችሁ፤ ሌላው ቢቀር፥ እባካችሁ በጋራ ሀገራችሁ በጋራ አብራችሁ የምትኖሩበትን ዘዴ ፈልጋችሁና ብልሀትም አበጅታችሁ፥ በጋራ ለመኖር ተስማሙ እያለ የሚመክራቸው። በጋራ ሀገራችሁ በጋራ ልትኖሩባት ስትችሉ፥ በጋራ ለመኖር የሚያስችላችሁን ሁኔታ አታበላሹት ነው የሚላቸው። ባጭሩ፥ በፖለቲካችሁ የጋራ ተግባር ለመፈፀም ካልቻላችሁ፥ ሀገሪቱ የሁላችሁም የጋራችሁ ነችና፥ በጋራ እንኑርባት ብላችሁ ወስኑ። ሌላው ቢቀር ይህን ብቻ እንኳን ማድረግ ከቻላችሁ፥ ለሀገራችሁና ለሕዝባችሁ ታላቅ ተግባር እንዳከናወናችሁ ይቆጠርላችኋል እያላቸው ነው። በጋራ ሀገራችሁ በጋራ እንዳትኖሩ የሚከፋፍላችሁን፥ ይህን የጋራ ሀገራችኚን የጋራ ጠላት የሆነውን ከፋፋዩን ሥርዓት በጋራ ማስወገድ አለባችሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የፖለቲካ ድርጅቶችን በመማፀን ላይ የሚገኘው፥ <u>የጋራ ብሄራዊ የትግል አጀንዳ አዘጋጅታችሁ በጋራ በመታገል፥ከዘረኞች ሥርዓት ገላግሉኝ እያለ ነው። ይህ ነው ወቅታዊው የሕዝቡ ጥሪና ተማፅኖ ።</u> ሀገሪቷ ከአምባገነኖች ተላቀቀችም አልተላቀቀች፥ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች፥ በጋራ ተስማምተው በጋራ ሀገራቸው በጋራ የሚኖሩበትን ሁኔታ እያስተካከሉ መሄድ የግድ ማለቱን በግድ መረዳት አለባቸው። ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ካልተረዱ ደግሞ የሚያስከትለውን ሁለንተናዊ ችግር መገንዘብ የሚያዳግት ሊሆን አይችልም።

ለጋራ ጉዳይ የጋራ ባለቤትና የጋራ ኃላፊነት ከመፍጠር የበለጠ ሌላ ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣ ዘዴ አይኖርም። ይህንን መሠረታዊ ቁም ነገር እንደ ሌለ በመቁጠር፥ የግልና የቡድንን ምኞትና ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ሲባል የሚደረገው ግብዝነት፥ ለሀገር ቀርቶ፥ ለግልም እንደማይጠቅም ማነኛቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች አፅንዖት በመስጠት ሊረዱት ይገባል። አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችም ይሁኑ፥ ወይም ሌሎች ግለሰቦች፥ በመገናኛ ብዙኃንም ይሁን በየሕዝባዊ ስብሰባዎች የሚሰጡት አስተያየትም ሆነ ንግግር፥ ሊያስከትል የሚችለውን ሁለንተናዊ አስተጋብዖ በሁለንተናዊው መልኩ በቅጡ ሊያጠኑት ይገባዋል። ከሁሉ አስቀድሞ፥በግንዛቤ ውስጥ ሊታይ የሚገባው፥

በሕዝብ አንድነትና ዘለቄታ ጥቅም ዙሪያ ሊካተቱ በሚችሉ ሁኔታዎች ላይ መስማማት ይገባል:: ዛሬ የወያኔ መሪዎች የህጋዊ ተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን አብዛኛዎቹን አስረዋል:: የገደሏቸውና ያሳደዷቸውም አሉ:: መዳረሻቸውንም ያጠፏቸው ቁጥር አይታወቅም:: ይህ ደግሞ የማይጠበቅ አልነበረም:: መለስና ተባባሪዎቹ የሚሰሩትን የሚያውቁ ቡድኖች ናቸው:: ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የሚሰጡት፥ የድርጅት መሪዎችን፥ ከተቻለ ማጥፋት፥ ካልሆነላቸው ደግሞ መከፋፈልና ማዳከም ነው:: ይህ ደግሞ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ አይደለም:: ከዚህም ሌላ አንድ መሠረታዊ ዕምነትና የማይካድ ሐቅ እንዳለ መታወቅ አለበት:: ምንም ምን ይሁን፤ ባዕዳንና የወያኔ መሪዎች ይተባበሩም ያድሙ፥ የተቃዋሚ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ዛሬም እንደ ጥንቱ፥ በጋራ ሀገራቸው በጋራ ለመኖር የወሰኑ መሆናቸውና ይህንም ዕውን ለማድረግ በሚያደርጉት ትግል ምንም ምድራዊ ኃይል የማይበግራቸው መሆኑን ነው::

በበኩላችን ዛሬም ይሁን ነገ፥ ቅድሚያ የምንሰጠው ለሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም፥ ለሕዝባችን ዘለቄታዊ አንድነትና ሀገራዊ ልዕልና ነው:: ይህን መሠረታዊ ዕምነት ከሚጋሩልን ጋር ሁሉ እንተባበራለን:: በጋራ ሀገራችንም፥ በጋራ ሊያኖረን በሚያስችለን በማነኛውም ጉዳይ ሁሉ ዕውን እስኪሆን ተግተን እንሠራለን:: ለዚህ ዓላማና ግብ ዕንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉትን ሁሉ እንቃወማለን:: የቅድሚያ ምኞታችንና ዓላማችን፥ ሀገራችንን ከወደቀችበት አዘቅት ማዳን ነው:: ሕዝባችን በብሄረሰብ፥ በኃይማኖት፥ በቋንቋና ወይም ደግሞ በሌሎች ሰው ሰራሽ ልዩነቶች እንዳይከፋፈል የተቻለንን ሁሉ የመከላከልና የመቃወም ግዳጅና ኃላፊነት አለብን:: ለእነዚህ መሠረታዊና ዓበይት ሀገራዊ ጉዳዮች ትኩረት የምንሰጠውም፥ ለአርምሞ ግንዛቤ እንዲሆን ብቻ ሳይሆን፥ መሠረታዊ ዕምነትም ስለአለን ነው:: ሀገርና ሕዝብ ከሌሉ፤ ማለትም፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከሕዝቧ ጋር ከሌለች፥ ሌላው ሁሉ ትርፍ መሆኑ የትግላችን ፅኑ መሠረት ስለሆነ ነው:: ተልዕኳችንም ይኸው ነው:: ይህ ዕምነታችን ደግሞ የትግላችን መነሻና መድረሻ የታሪካችን አልፋና ዖሜጋ፥ ብሎም፥ የመሥዋዕታችን ራዕይና ግብ በመሆኑ ነው:: ከማነኛውም በላይና በበለጠ ደረጃ፥ የኢትዮጵያና ሕዝቧ በሰላም አብሮ መኖር ለእኛ ልዩ ትርጉምና ህላዌ አለው:: ኢትዮጵያ ሀገራችንንም ሆነ ሕዝባችንን እንዳማራጭ አናያቸውም:: ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ የሚሉትን ከፋፋዮች ሁሉ አምርረን ስንታገላቸው የቆነውም በዚህ ፅኑ ዕምነታችን ነው:: ወደፊትም ቢሆን ይህንን የፀና ዕምነታችንን ሊያስለውጠን የሚችል ምድራዊ ኃይል ይኖራል ብለን አናምንም::

ይህ ከሆነ ዘንዳ፥ ከሰባ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያላት ሀገራችን፥ የሁላችንም የጋራ ቤታችን መሆኗን አምነን መቀበል አለብን:: ሕዝብን በብሄረሰብ ሆነ በክልል፥እንዲሁም ፖለቲካ ድርጅቶችን ደግሞ፥ በዕምነታቸውና በታሪካቸው፥ በይዘታቸውና በዓላማቸው እየፈረጁ መከፋፈል አይጠቅምም እንላለን:: በተለያዩ ሀገሮች፥ የተለያዩ ፕሮግራሞች፥ ዓላማና ግብ ያላቸው ብዙኃን የፖለቲካ ድርጅቶች፥ በጋራ ሀገራቸው በጋራ ተስማምተው እንደሚኖሩ እናውቃለን:: አንዱ ሌላውን ለማጥፋት የሚያደርገው ስልትና ድርጊት ግን

ጉዳት እንጂ ጥቅም ሲያመጣ አልሰማንም፥ አልተገነዘብንም፡፡ ፡፡ ምክንያቱም፥ ይህን ክስተት ቢከተሉ፥ አጥፊና ጠፊ የሚሆኑ መሆናቸውን አበክረው ስለሚረዱ ይህንን አይሞክሩትም፡፡ በነፃ ተወዳድረው ግን አንዱ አቸናፊ ሲሆን ሌላው ችንፈቱን አምኖና ተቀብሎ በሰላም መኖር መቻል አለበት፡፡ ለዚህ ሁሉ ዋና መሠረቱ ግን፥ የዴሞክራሲ ሥርዓት መስፈን ነው፡፡ መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ፥ የሕዝቡን ድምፅ ቀምተው በሥልጣን ለመቆየት መወሰናቸው ብቻ ሳይሆን፥ የተቃዋሚ ድርጅቶችንም ጭምር ለማጥፋት በመጣር ላይ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ዛሬ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የጠማት ሀገር ነች፡፡ በመሆኑም የአምባገነን ሥርዓት ነቅቅሎ ለመጣል ያለው ምርጫ ያው አንድ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም የተቃዋሚንው ጎራ አጠናክሮ፥ አብሮና ተባብሮ መቆም ነው፡፡ ይህ ጉዳይ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስኪሰለቸው ድረስ ተደጋግሞ ተደጋግሞ የተነገረ በመሆኑ፥ ብዙ ማለት አይቻልም፡፡ በዴሞክራሲ ሥርዓት መተዳደር የታደሉ ሀገሮች፥ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ከነልዩነቶቻቸው ተስማምተው በጋራ ሀገራቸው በጋራ ለመኖር ከቻሉ፤ በእኛይቱ ኢትዮጵያም ቢሆን፥ ይህ ሁኔታ የማይኖርበት ምክንያት የለም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፥ አንድ መሠረታዊ ሀቅ መኖሩን ለማስመር እንፈልጋለን፡፡ ተወደደም ተጠላ፥ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ገፅታና ነባራዊ ሁኔታ በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ግዴታቸው መሆኑን፥ ለፖለቲካ ሥልጣን እንታገላለን የሚሉ ድርጅቶች ሁሉ ሊያውቁት የሚገባቸው የፖለቲካ ሀቅ መሆኑን ነው፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን የአያሌ ብሔር-ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን አምነው ካልተቀበሉ፥ እንዲያው ከመጀመሪያው ትልቅ መሠረታዊ የአመለካከት ችግር አለ ማለት ነው፡፡ የተለያዩ ብሔረሰቦች መኖር ደግሞ ጥንካሬ እንጅ፥ ድክመት እንዳልሆነ፥ ብልፅግና እንጅ ድኅነት እንዳልሆነ፥ መታደል እንጅ አለመታደል እንዳልሆነ፥ ጌጥና ኩራት እንጅ ኃፍረት  እንዳልሆነ፥ ሁሉም አውቆ የጋራ ሀገራችን  የጋራ መኖሪያችን መሆኗን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል፡፡  ይህን መገንዘብ ከተቻለ፥ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት የሚያደረገው ከንቱ ሙከራ ዋጋ ቢስነቱ ታውቆ የሚወገድ ይመስለናል፡፡  ያለፈው እርስ በእርስ መጠፋፋትና ሀገርን የመጉዳት ክስተት መቆም አለበት፡፡ በብሄረሰብ መከፋፈል ደግሞ፥ ሀገር ጎድቶ ወያኔን የሚጠቅም ስለሚሆን፥ በመከባበርና በእኩልነት ከጠባብነትና ከትምክህት ርቆ በጋራ ሆኖ፥ የጋራ ሀገርን ላመዳን መዋደቅ ያስፈልጋል፡፡ የጦርነትን ምንንት በተመለከተ ደግሞ፥ ከራሱ ከባለቤቱ፥ ከባለጉዳዩ፥ ከጦርነቱ ተሳታፊና ተጠቂ ከሆነው፥ከሕዝቡና ከወታደሩ የበለጠ የሚያውቅና የሚጠላው ያለ አይመስለንም፡፡  በሞተ -ከዳ የሚመጣውና የሚሾመው በሚገባ አያውቀውም፡፡ የፖሊቲካ ትግልን መራራነትና መስዋዕትንም በሚገባ ሊያውቀው የሚችለው ፥ ለረዥም ዓመታት በትግሉ የተሳተፈውና አይከፍሉ መሥዋዕት የከፈለው ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ይመስለናል፡ በጋራ ሀገራችን በጋራ  ለመኖር ስንል ብዙ መከራን ስንቀበል የቆየነው፡፡

በፖለቲካው የበሰሉ ክፍሎች፥ በድርጅቶች መሀል የፕሮግራም ልዩነት መኖሩ ፀጋ መሆኑ ይገባቸዋል፡፡ በሀገር ህልውና ጉዳይ፤ ሀገርን ከጥፋት በማዳኑ ላይ ስምምነት እሰካለ ድረስም፥ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ የሚከሰቱ የተለያዩ አቋሞች

የሚያጋድሉ አይደሉም:: ነፃና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን፥ ማረጋገጥ ከቻልን፥ ሕዝብ በነፃ ምርጫ የሚበጀውን ይመርጣልና የሚያስጨንቅ አይሆንም:: ከወዲሁ፥ ከእኔ ሌላ ድርጅት ለአፈር ማለት አይጠቅምም:: በራስ ፕሮግራምና ሥራ መሠረት ድጋፍን ከማግኘት ፈንታ ፥በሌላ ድርጅት ላይ አፀያፊ ዘመቻ በመክፈት ተከታይ ለማግኘት መሞከሩ ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል:: ወያኔ በሀሳብና በቋም የተቃረነውን ድርጅት ሁሉ ጠላት ብሎ ለማውደም ሲጥር ታይቷል:: ዛሬም የተለየ አቋም የለውም:: ይህ ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲነት መሆኑ በገሀድ የታየ ነው:: ለሀገራችን የሚበጃት አንድ ወይም ሁለት ድርጅት ብቻ ነው ብሎ መወስን -መደንገግ የሚቻል አይመስለንም:: የድርጅቶችን ህልውና ወሳኝ ሕዝብ ብቻ ነው:: የሚደግፋቸውን አቅፎ በማጠናከርና የማይፈልጋቸውን ደግሞ ድጋፍ ነስቶ በማጫጫት ችግሩን ያስወግዳል:: ስለዚህም ዛሬ አንዳንዶች ከአንድ ወይም ሁለት ድርጅት ውጪ መኖር የለበትም:: የብሄረሰብ ድርጅቶችም መኖር የለባቸውም የሚሉት ጠቃሚ ሳይሆን፥ ጎጂና መብትን ረጋጭ ነው:: ድርጅቶችም፥ እነሆ በሥራችን በተግባራችን ፍረዱን ማለት አለባቸው እንጂ፥ በተመሠረቱ ማዕግስት በነባር ድርጅቶች ላይ የጥላቻ ዘመቻ መክፈት የለባቸውም:: ዘመቻ ከተከፈተማ የተጠቃው ደግሞ ሊከላከል መመለሱ የግድ ይሆናል:: ግርግሩም ለወያኔ ሰርጎ-ገቦች አንዱን ወይም ሌላውን ደጋፊ መስለው፥ ረብሻን እንዲፈጥሩ/ እንዲያባብሱ በር ይከፈትላቸዋል:: ይህን ጠንቅቆ መረዳት ይገባል::

በአሁኑ ወቅት በተቃዋሚ ድርጅቶች መሀል ልዩነትን እያረገቡ የመቀራረብ አዝማሚያ ይታያል:: ይህ መበረታታት አለበት:: - ድርጅቶች ቅራኔዎችን አርግበው፤ ነገር አባባሾችን አስወግደው፤ የወያኔ ሰርጎገቦችን አሳፍረውና መንጥረው ለጋራ ሀገራቸው በጋራ መቆም አለባቸው:: አንዱ የሌላው ጠላት አይደለምና:: ዛሬ በድርጅቶች መሀል ቅራኔ በማባባሱ ተልዕኮ ላይ ተሰማርተው የሚገኙት በተለይም በባዕድ ሀገር ያሉ ግለሰቦችና በድረ ገፅ (ኢንተርኔት) አማካኝነት መርዛቸውን የሚረጩት ናቸው:: የድርጅቶች ደጋፊ መስለው ቅራኔ ያባብሳሉ:: በወንጀል እንጠየቃላን ብለው የፈሩና በከሀዲነት ሕዝብ ለፍርድ ያቀርበናል ብለው የሰጉትም ቢሆኑ፥ አጥፊ ዘመቻቸውን ከፍተዋል:: ይቅር ለእግዜር ይስፈን ቢባልም፤ በዋናው ጠላት ላይ ማተኮር ቢገባም፥ ሰላም ከመጣ ጉዳችን ፈላ ባይ ናቸው:: የመልካም ዜጎችን መልካም ስም በማጥፋት የተሰማሩ ግለሰቦችና ቡድኖች፥ ከዚህ እኩይ ተግባራቸው ሊቆጠቡ ይገባል:: ይህ ካልሆነ፥ በራሳቸው ላይ እባብ እየጠመጠሙ መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው:: እንዲህ ዓይነት በጥባጮች የበላይነትን እንዳያገኙ መታገል አለብን:: የድርጅት መሪ መባል ያለውን ሀላፊነት መረዳት ያቀታቸውም ደግሞ፥ አደብ እንዲገዙ፥ አነጋገራቸውን እንዲያርሙ፥ ትዕግስትና ብስለትም እንዲኖራቸው ማሳሰብ ይገባል:: በነገር ናዳና በአሉባልታ ዘመቻ ጠንካራ ድርጅት አይፈርስምና ከዘለፋው ቀነስ፥ ከትግሉ ጠበቅ ልንላቸውም ይገባል:: ይህን ምክር አልሰማ ካሉና በጎጂ ዘመቻቸው ከቀጠሉ ግን፥ ራሳቸውንም ሀገራችንንም ጎድተው፥ ለወያኔ እንደሚጠቅሙ ማወቅ አለባቸው:: የደርግንና የወያኔን ዘለፋ ተቀብሎ በድርጅቶች ላይ መዝመት ለትግሉ አይበጅም:: ድርጅቶች፥ እርስ በርስ ከመነታረክ ይልቅ፥ የጋራ ሀገራችንን ለማዳን

ትዕግሰቱም፣ ሆደ ሰፊነቱም፣ብርታቱም ፅናቱም ይኖራቸው ዘንድ እንመኛለን። ባንስማማም ለጋራ ሀገራችን ልዩነቶቻችን አቻችለንና በሕዝብ ወሳኝነት አምነን በገራ መታገል አሁንም እንችላለን።

ለከፋፋዮች አንመች። ለሰርጎገቦች አንመች። ማን ይሻላል? የትኛውስ ይበጃል? እና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ሕዝብ በነፃ ምርጫ እንዲወስን፥ የመለስን አገዛዝ በማስወገድ፥ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ እንታገል።